# Learning by Ear 2013

**«መንታ መንገድ ላይ ያለ ትውልድ–«መዘዙን መቀበል»**

EPISODE 11: **መጥፎ ግርምቶች**

**AUTHOR: James Muhando**

**EDITORS: Friederike Müller, Daniel Pelz, Madelaine Meier**

**COPY EDITOR: Charlotte Collins**

**List of characters by scene:**

**<u>INTRO/OUTRO:</u> NARRATOR**

**<u>SCENE 1: ዶክተር ሮቤልACCOMPANIES ምህሬት HOME</u>**

- **ምህረት (F, 15)**
- **ዶክተር ሮቤል (M, 50s)**
- **ወ/ሮ ሉሊት (F, 40)**

**<u>SCENE 2: ትዕግስት TELLS ON ምህሬት</u>**

- **ርዕሰ መምህርት ሰብለ (F, 50)**
- **ትዕግስት (F, 15)**
- **አቶ ጃለታ (M, 45)**

**<u>SCENE 3: ትዕግስት TALKS TO ንጉሴ</u>**

- **ትዕግስት(F, 15)**
- **ንጉሴ (M, 16)**

**<u>SCENE 4: ንጉሴ’S FATHER IN ርዕሰ መምህርት ሰብለ’S OFFICE</u>**

- **ርዕሰ መምህርት ሰብለ (F, 50)**
- **አቶ ጃለታ (M, 45)**

**INTRO**

## 1. NARRATOR:

ጤና ይስጥልን ዉድ የበማድመጥ መማር ተከታታዮች። ይህ "መንታ መንገድ ላይ ያለ ትውልድ" የተሰኘው ተከታታይ ድራማችን ነዉ።—«መዘዙን መቀበል» በተሰኘዉ ሁለተኛው ዙር ድራማ 11ኛ ክፍል ላይ ደርሰናል። ቀደም ሲል የ16 አመቱ ንጉሴን ወላጆቹ መንገድ ዳር ተዘርሮ ሲያገኙት መደናግጣቸውን ተመልክተን ነበር።

## 2. EPISODE 6, LINES 70-72:

*አቶ ጃለታ: ንጉሴ? ተጎድተሀል?*

*ንጉሴ: እኔ? ልጎዳ? በፍፁም! ሀይለኛውን ንጉሴን ማንም ሊጎዳ አይችልም!*

*አቶ ጃለታ: ሰክርሀል እንዴ?አንተ ልጅ ምን ሆነሀል?*

## 3. NARRATOR:

ንጉሴ አሁንም ድረስ ምህረትን ያፈቅራታል። ግን ለእሷ ምርጫዋ ዳንኤል ሆኖ፣ ከእሱም ጋ ተኝታ አርግዛለች። ጓደኛዋ ትዕግስት ደግሞ ፅንሱን እንድታስወርድ ትፈልጋለች። በአንፃሩ ምህረት የትዕግስትን ምክር አልተቀበለችም።:

## 4. EPISODE 10, LINES 29-31:

*ምህረት: አቁሚ ትዕግስት።. (...)አንቺ ፅንሱን እንዳስወርድ እና ዶክተር ዘሪሁን ጋ እንድሄድ ስትመክሪኝ ነበር። ይህንንም ያደረግሽው ደንበኛ ስታመጪለት ገንዘብ ስለሚከፍልሽ ነው።*

*ትዕግስት: ምህረት የምታወሪውን አታውቂም ፅን--*

*ምህረት: ሂጂ ትዕግስት! ጥፊ ከዚህ! (…)*

**5. NARRATOR:**

**ይህ በእንዲህ እንዳለ የምህረት ወንድም ብሩክ በጣም ታሞ ነበር። ምህረትም እናቷን ሳታስፈቅድ ታናሽ ወንድሟን ሆስፒታል ዶክተር ሮቤል ዘንድ ወስዳዋለች። የዛሬው ጭውውት ክፍል «መጥፎ ግርምቶች» ይሰኛል። ጭውውቱ የሚጀምረው ምህረት ወደ መኖሪያዋ አደታንዲካ የድሆች ሠፈር ስትመለስ ነው— እንግዳ ይዛ መጥታለች።….**

**<u>SCENE 1: ዶክተር ሮቤልACCOMPANIES ምህሬት HOME</u>**

**6. ATMO: TANDIKA SLUMS, OUTSIDE ምህሬት'S HOME, DAYTIME**

**7. SFX: TRIES TO OPEN LOCKED DOOR**

**8. ምህረት:** **ውይ በሩ ተቆልፏል።**

**9. SFX: KNOCK ON DOOR**

**10. ምህረት:** **እማ እኔ ነኝ ምህረት።**

**11. SFX: WATER SLOSHING AS SOMEBODY BATHES (HEARD FROM INSIDE)**

**12. ወ/ሮ ሉሊት:** **(shouts from inside) ቆይኝ ገላዬን እየታጠብኩ ነው። ስጨርስ አንቺ እና ብሩክ የት ሄዳችሁ እንደነበር ትነግሪኛለሽ። እኔ እዚህ በጭንቀት ልሞት ነበር።**

**13.** ምህረት: እሺ እማ! **(to ዶክተር ሮቤል, a little embarrassed)** ይቅርታ ዶክተር - ቤታችን አንድ ክፍል ነው። አልፎ አልፎም እንደ ገላ መታጠቢያ ቤትም እንጠቀምበታለን።

**14.** ዶክተር ሮቤል: ምንም ችግር የለም ምህረት። ሀኪም ከመሆኔ በፊት እንደዚህ ተመሳሳይ ሰፈር ውስጥ ነው የኖርኩት።

**15.** ምህረት: በእውነት?

***KW BEGIN***

**16.** ዶክተር ሮቤል: አዎ! ድሮ ኮሌጅ እያለሁ ለሶስት ሆነን ነበር አንድ ክፍል ቤት ውስጥ የምንኖረው። እኛም ታድያ ክፍላችንን በፈረቃ መታጠቢያ ቤት አድርገን እንታጠብበት ነበር። ታዲያልሽ መጨረሻ ላይ የሚታጠብ እድለ ቢስ ነበር። ምክንያቱም ሲጨርስ ወለሉን መወልወል እና ውሃውን ማድረቅ ነበረበት።

**17.** ምህረት: **(laughs)** ስለእዚህ መጀመሪያ ለመታጠብ ትግል ነበር በሉኛ?

**18.** ዶክተር ሮቤል: **(laughs too)** እንደዛ ማለት እንኳን አልችልም። ሌሎቹ እንቅልፋም ነበሩ። እኔ ብቻ ነበርኩ ከሌሊቱ 10 ሰዓት ከእንቅልፌ መነሳት የነበረብኝ።

**19.** ምህረት: **(laughs even more)** በስመአም! ለምንድን ነው እንደዚህ በሌሊት መነሳት የነበረብዎ?

**20.** ዶክተር ሮቤል: ምክንያቱም ኮሌጅ መሄድ ነበረብኝ። ትምህርት ቤቱ ደግሞ 12 ኪ. ሜ ርቆ ነበር የሚገኘው።

**21.** ምህረት: ታድያ ለምን ለኮሌጁ ቅርብ የሆነ ቦታ ለመኖር አልሞከሩም?

**22.** ዶክተር ሮቤል: አየሽ በወቅቱ እዛ አካባቢ ያሉት ቤቶች ውድ ነበሩ። መክፈል አለመቻሌ ብቻ ሳይሆን --

***KW END***

**23. SFX: DOOR OPENS**

**24.** ወ/ሮ ሉሊት: ምህረት! ብሩክ የታለ?... (**to** ዶክተር ሮቤል) ውይ - ሰላም! ጤናስጥልኝ...? እንግዳ እንደመጣ አላወቅኩም ነበር።

**25.** ዶክተር ሮቤል: ዶክተር ሮቤል እባላለሁ። እርሶ የምህረት እና የብሩክ እናት መሆን አለብዎት! ወደ ውስጥ ገብቼ ላናግርዎ እችላለሁ?

**26.** ወ/ሮ ሉሊት: **(hesitates)** እ -እሺ. ጥሩ። ይቅርታ ወለሉ ትንሽ ረጥቧል።

**27.** ዶክተር ሮቤል: ምንም አይደል።

**28. SFX: FOOTSTEPS (3 PEOPLE) ON WET CONCRETE FLOOR**

**29. SFX: DOOR CLOSED**

**30. ATMO: TANDIKA SLUMS AT DAYTIME HEARD FROM INSIDE**

**31.** ወ/ሮ ሉሊት: **(whispers to** ምህረት**)** ሰውየው ማናቸው? ወንድምሽ የታል? ቅዱስ በጠዋት ነው ከሱ ጋ ወጥተሽ መሄድሽን የነገረኝ።

**32.** ምህረት: እእእ...

**33.** ዶክተር ሮቤል: **(clears his throat)** የምህረት እናት እዚህ የመጣሁት ከእርሶ ጋ ስለ ብሩክ ለመነጋገር ነው።

**34.** ወ/ሮ ሉሊት: ብሩክ ምን ሆነ? ምን አድርጎ ነው? የፈጣሪ ያለ! በቃ ሌላ ችግር አይንገሩኝ እባክዎ።

**35.** ዶክተር ሮቤል: ይረጋጉ የምህረት እናት። ብሩክ ደህና ነው... ምንም አይል ይሻለዋል። እድሜ ለምህረት አሁን ሆስፒታል ነው ያለው--

**36.** ወ/ሮ ሉሊት: **(angry)** ሆስፒታል? ምህረት ስለዚህ ምን ብየሽ ነበር?

**37.** ምህረት: ይቅርታ እማዬ ግን ብሩክ እንደዛ ሲሰቃይ ዝም ብዬ መመልከት ስላልቻልኩ ነው።

**38.** ወ/ሮ ሉሊት: አንቺ ልጅ፤ ሰሞኑን የሚሉሽን የማትሰሚ ልጅ ሆነሻል። እኔንጃ ምን እንዳስለከፋሽ። ባለውቃቢው እንዳሉት-

**39.** ዶክተር ሮቤል: **(cuts in)** የምህረት እናት ። እባክዎን ያድምጡኝ። ልጅዎ ማድረግ ያለባትን ነው ያደረገችው። ብሩክ ሊሞት ሁሉ ይችል ነበር። የስራ ባልደረቦቼ አንዳንድ ናሙና ወስደው በአሁኑ ሰዓት እየመረመሩት ይገኛሉ። የምንጠረጥረው TB ነው።

**40.** ወ/ሮ ሉሊት: ምንድን ነው ደሞ እሱ?

**41.** ዶክተር ሮቤል: TB ማለት ቱበርክሎሰስ። ወይንም በተለምዶ የሳንባ ነቀርሳ የምንለው ነው። በጣም አደገኛ ነው። በአግባቡ ካልታከሙት ሊገል ይችላል።

**42.** ወ/ሮ ሉሊት: **(shocked)** ምን? ብሩክ! ልጄ! ግን ለምን… ማለቴ እንዲህ… ለሚያስለው ምክንያቱ ይሄ TB የሚሉት ጉድ ነው ማለት ነው?

**43.** ዶክተር ሮቤል: አዎ ይመስለኛል። TB የሚከሰተው አብዛኛውን ጊዜ ሳንባችንን በሚነካ ባክቴሪያ ነው። በአንዴ ሊሰራጭ ይችላል። ይሄ በሽታ የያዘው ሰው ከሳለ ወይንም ካነጠሰ ባክቴሪያው ወደምንተነፍሰው አየር ይገባና ሌሎች ሰዎች ይህንን አየር ሊተነፍሱ ይችላሉ። እና አንዳንዴ እንደውም ሰዎቹም ሊያዙ ይችላሉ። ለዚህ ነው መላው ቤተሰቡ መመርመር ያለበት።

***KW BEGIN***

**44.** ወ/ሮ ሉሊት: ምን? እያሉኝ ያሉት እኛም ተይዘን ይሆናል ነው? እና ታዲያ ይህንን ሁሉ ወጪ ማን ነው የሚሸፍነው?

**45.** ዶክተር ሮቤል: የምህረት እናት ይህ አያሳስብዎ። እንደ በርካታ የአፍሪቃ አገሮች ሁሉ የ TB ምርመራ በኪሲምባ ነፃ ነው።

**46.** ምህረት: **(clears her throat)** ዶክተር አሁን ወደ ት/ቤት መሄድ እችላለሁ?

**47.** ዶክተር ሮቤል: አዎ ናሙናሽን እስከወሰድን ድረስ ትችያለሽ ምህረት። ግን ናሙናው TB እንዳለብሽ ካሳየ ተመልሰሽ ወደ ሆስፒታል መምጣት ይኖርብሻል። ይህን ታውቂያለሽ አይደል?

**48.** ምህረት: አዎ፤ እሺ።

**49.** ዶክተር ሮቤል: አሁን እንሂድ የምህረት እናት?

***KW END***

**50. MUSICAL INTERLUDE**

**SCENE 2: ትዕግስት TELLS ON ምህሬት**

**51. ATMO: IN THE SCHOOL CORRIDOR (BREAKTIME SOUNDS HEARD FROM INSIDE)**

**52. SFX: KNOCK ON DOOR**

**53.** ርዕሰ መምህርት ሰብለ: **(from inside her office)** ይግቡ!

**54. SFX: DOOR OPENED AND CLOSED**

**55. SFX: FOOTSTEPS - ትዕግስት ENTERS**

**56.** ርዕሰ መምህርት ሰብለ: አ ትዕግስት! ተቀመጭ። ምን ልርዳሽ?

**57. SFX: CHAIR PULLED, CLOTHES RUSTLE**

**58.** ትዕግስት: ርዕሰ መምህርት ሰብለ አንድ ነገር ልነግርዎ ፈልጌ ነበር።

**59.** ርዕሰ መምህርት ሰብለ: እየሰማሁ ነው ቀጥይ።

**60.** ትዕግስት: ስለ ምህረት ነው።

**61.** ርዕሰ መምህርት ሰብለ: ስለ ምህረት ምን?

**62.** ትዕግስት: ዛሬ ትምህርት ቤት አልመጣችም።

**63.** ርዕሰ መምህርት ሰብለ: አዎ። አስተውያለሁ። ለምን እንደሆነ ታውቂያለሽ?

**64.** ትዕግስት: ባለፉት ቀናት ሲያስመልሳት ነበር።

**65.** ርዕሰ መምህርት ሰብለ: **(concerned)** ታማለች ማለት ነው? የትምህርት ቤቷ ነርስ አይታታለች?

**66.** ትዕግስት: አይ! እንደዛ አይደለም… አርግዛለች።

**67.** ርዕሰ መምህርት ሰብለ: ምን?

**68. SFX: KNOCK ON THE DOOR, DOOR OPENS.**

**69.** አቶ ጃለታ: **(from the door)** ይቅርታ ስላቋረጥኳችሁ። ርዕሰ መምህርት ሰብለ ሊያናግሩኝ ፈልገው ነበር?

**70.** ርዕሰ መምህርት ሰብለ: አ – አዎ አቶ ጃለታ እባክዎን ይግቡ

**71. SFX: STEPS** አቶ ጃለታ **APPROACH**

**72.** ርዕሰ መምህርት ሰብለ: **(to** ትዕግስት**)** ትዕግስት ወደ ውጭ ወጣ በይ። ስለዚህ ከማንም ጋ እንዳታወሪ እሺ?! ለኔ ተይው።

**73.** ትዕግስት: እሺ ግን እኔ እንደነገርኩዎ እንዳይነግሯት --

**74. SFX: CHAIR SCRAPING AS** ትዕግስት **GETS UP**

**75.** ርዕሰ መምህርት ሰብለ: **(cuts her short)** እሱ አያሳስብሽ። መምጣትሽ መናገርሽ ትክክል ነበር።

**76.** ትዕግስት: አመሰግናለሁ ርዕሰ መምህርት ሰብለ

**77. SFX: FOOTSTEPS AS ትዕግስት LEAVES, DOOR CLOSING.**

***KW BEGIN***

**78.** ርዕሰ መምህርት ሰብለ: **(sighs)** አቶ ጃለታ ይኸው እንግዲህ ትምህርት ቤትን ማስተዳደር ቀላል አይደለም። ግን ይኼን ልነግርዎ አይደለም እዚህ ድረስ የጠራውዎ። ስለልጅዎ ንጉሴ ከእርስዎ ጋ መነጋገር ፈልጌ ነው።

**79.** አቶ ጃለታ: ንጉሴ አሁን ደግሞ ምን አደረገ?

**80.** ርዕሰ መምህርት ሰብለ: እባክዎን ይቀመጡ።

**81. SFX:** አቶ ጃለታ **SITS DOWN ON WOODEN CHAIR**

***KW END***

**82. MUSICAL INTERLUDE**

**OR FADE FROM OFFICE TO CORRIDOR ATMO**

**<u>SCENE 3: ትዕግስት TALKS TO ንጉሴ</u>**

**83. SFX: BONGO ACADEMY, INTERIOR AT BREAKTIME, ON CORRIDOR**

**84. SFX:** ትዕግስት**’S FOOTSTEPS**

**85.** ትዕግስት: **(Loud whisper)** ሄይ ንጉሴ? አንዴ ጠብቀኝ!

**86. SFX: FOOTSTEPS STOP**

**87.** ንጉሴ: **(not interested)** ታድያስ ትዕግስት?

**88.** ትዕግስት: ለምን እንደሌሎቹ ለዕረፍት ውጪ አልወጣህም? ወይንስ አባትህን እየጠበክ ነው? ካልተሳሳትኩ አሁን ርዕሰ መምህርቷ ቢሮ አይቻቸዋለሁ። ...

**89.** ንጉሴ: የማ የኔ አባት? አይ ሊሆን አይችልም። ዛሬ ጠዋት እዚህ ስለመምጣቱ ምንም ያለው ነገር የለም። መፀዳጃ ቤት ሂጄ መመለሴ ነው።

**90.** ትዕግስት: ለማንኛውም... አንድ ትኩስ ዜና ይገፎልህ መጥቻለሁ

***KW BEGIN***

**91.** ንጉሴ: **(not very interested)** ምንድን ነው?

**92.** ትዕግስት: **(loud whisper)** አለ የተባለ ጉድ ነው!

**93.** ንጉሴ: ምን ማለትሽ ነው?

***KW END***

**94.** ትዕግስት: እንዲህ ብልህ ምን ይሰማህል? ያንተ **(ironically)** ምርጥ ጓደኛ ዳንኤል ከቦንጎ አካዳሚ ሊባረርልህ ነው።

**95.** ንጉሴ: **(now interested)** ትቀልጃለሽ?

**96.** ትዕግስት: እየቀለድኩ አይደለም።

**97.** ንጉሴ: ምን አድርጎ?

**98.** ትዕግስት: በቅርቡ የሆነች ልጅን አስረግዞ።

**99.** ንጉሴ: ምን ? ማንን? የእዚህ ትምህርት ቤት ልጅ ናት?

**100.** ትዕግስት: እእእምምም!

**101.** ንጉሴ: ንገሪኝ! ማን ናት?

**102.** ትዕግስት: ምህረትን!

**103.** ንጉሴ: **(totally shocked)** ምን? የምርሽን ሊሆን አይችልም! ምህረት እርጉዝ ናት?

***KW BEGIN***

**104.** ትዕግስት: ነች! እራሷ ነች የነገረችኝ… ና! ወደውጪ እንሂድ! …ንጉሴ?

**105.** ንጉሴ: **(not listening, to himself)** ምህረት እርጉዝ ናት! ኖ በፍፁም ሊሆን አይችልም።

**106.** ትዕግስት: ኧረ ባክህ እሱን እርሳው ።

**107. SFX: HURRIED FOOTSTEPS AS ትዕግስት GOES AWAY**

***KW END***

**108.** ንጉሴ: **(to himself)** እኔ ይህን ማመን አልችልም።

**109. MUSICAL INTERLUDE**

**OR FADE FROM CORRIDOR TO OFFICE ATMO**

## SCENE 4: ንጉሴ'S FATHER IN ርዕሰ መምህርት ሰብለ'S OFFICE

**110. ATMO: ርዕሰ መምህርት ሰብለ'S OFFICE ATMO (BREAK)**

**111. SFX: PAPERS BEING SHUFFLED**

**112.** ርዕሰ መምህርት ሰብለ: **(official)** አቶ ጃለታ። ልጅዎ ንጉሴ ከዚህ ትምህርት ቤት ስነ-ስርዓት ያለው እና ጎበዝ ተማሪ ነበር። በጣም እንኮራበትም ነበር። ጎበዝ ነው።እና --

**113.** አቶ ጃለታ: **(proudly)** አዎ! ንጉሴ ጎበዝ ልጅ ነው።

**114.** ርዕሰ መምህርት ሰብለ: አዎ! ግን ከቅርብ ጊዜ አንስቶ የሆነ ጭንቀት እንዳለበት አስተውለናል። እና ውጤቱ እየቀነሰ ነው። ይህ ብቻ አይደለም…

**115.** አቶ ጃለታ: **(cuts in)** ርዕሰ መምህርት ሰብለ ፤ ንጉሴ ሰላም እንደሆነ አረጋግጥልዎታለሁ። ምን አልባት ልጁ ከባድ ጊዜ ገጥሞት ይሆናል --

**116.** ርዕሰ መምህርት ሰብለ: **(serious)** አቶ ጃለታ እባክዎን ያስጨርሱኝ።

**117.** አቶ ጃለታ: እሺ። ይቀጥሉ።

**118.** ርዕሰ መምህርት ሰብለ: **(sighs)** የትምህርት ቤታችን ጠባቂ ብዙ ጊዜ የትምህርት ቤቱ አጥር ስር ከለየለት እፅ አዘዋዋሪ ዱሩዬ ጋ አይቶታል። እና ምናልባት ልጅዎ ማሪዋና ያጨሳል ብዬ እሰጋለሁ።

**119.** አቶ ጃለታ: **(shocked)** ምን? የኛ ንጉሴ?

***KW BEGIN*** እንደው አልፎ አልፎ ቢራ ይጠጣ ይሆናል እንጂ። ማሪዋና?

**120.** ርዕሰ መምህርት ሰብለ: እዚህ ት/ቤት ውስጥ እፅ የመውሰድን ነገር በቀላሉ አናልፈውም፤ በጣም በከፍተኛ ሁኔታ ነው የምናየውው። እንደ ንጉሴ ወለጆች እናንተም ብትሆኑ እንደዛ ልታዩት ይገባል።

**121.** አቶ ጃለታ: በትክክል! ስለእዛ በደንብ እንደማነጋገረe አረጋግጥሎታለሁ።

***KW END***

**122.** ርዕሰ መምህርት ሰብለ: አቶ ጃለታ በጣም አዝናለሁ። ንጉሴን ከቦንጎ አካዴሚ አግደንዋል።

**123.** አቶ ጃለታ: **(even more shocked)** ምን?!

**124.** ርዕሰ መምህርት ሰብለ: በኋላ እኔው እራሴ እነግረዋለሁ። – ምንም አማራጭ የለንም። እፅን በተመለከተ ያለን አቋም ግልፅ ነው።

**125.** አቶ ጃለታ: **(to himself)** እኔ ይሄን አላምንም…

**126. <u>OUTRO- NARRATOR:</u>**

የንጉሴ አባት በጣም ደንግጠዋል። ይህንን ዜና ርዕሰ መምህርቷ ለንጉሴ ሲነግሩት እሱስ ምን ያደርግ ይሆን? በቦንጎ አካዴሚ ሌሎች ያልተጠበቁ ምን አይነት ነገሮችስ ታዳጊ ወጣቶቹን ይጠብቃቸዋል? ደስ የሚለው ዜና ይህንን በአጠቃላይ ለማወቅ እስከሚቀስለው የስርጭት ጊዜ መጠበቅ አያስፈልጋችሁም። … አልማዝን ለዳንኤል ምን እንዳቀደች ካዘጋጀችው የቪዲዮ ዘገባ ተመልከቱ። ቪዲዮውን የምታገኙት በድረገፃችን dw.de/lbe ላይ ነው። « መንታ መንገድ ላይ ያለ ትውልድ» የተሰኘውን ድራማችንም በተመለከተ በፌስቡክ ገፃችን ላይ ብትወያዩ ደስ ይለናል።እስከሚቀጥለው ጊዜ ደህና ሁኑ።